# በኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ አደጋ ወቅት የዲስትሪክቱ  የልጅ አሳዳጊ የገንዘብ ድጋፍና አሳዳጊነትን በተመለከተ ስላለው አቋም

**( ነሓሴ 30 ቀን 2021 የተሻሻለ)**


ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support)

ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support) ሲባል ምን ማለት ነው ?

ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support) ለማግኘት ብቁ የሚሆነው ማነው?

ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support) የሚከፍለው ማነው?

ለልጅ አሳዳጊ ድጋፍ ገንዘብ መስጠትን በተመለከተ፤ ፍርድቤቱ፤ የልጆቹ አሳዳጊ ማን መሆኑን የሚያረጋግጠው እንዴት ነው?

የልጆችን የአሳዳጊነት ገንዘብ እገዛ በሚመለከት፡ *የፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሌለ፤* አብዛኛውን ግዜ ከልጆቹ ጋር የሚያሳልፍ አዋቂ ሰው ነው እንደ አሳዳጊ የሚቆጠረው። ልጆቹ ከአባታቸውም ጋር ይሁን ከእናታቸው ጋር የሚያሳልፉት ግዜ እኩል ከሆነ ከሁለቱ ወላጆች የበዛ ገቢ ያለው ወላጅ ዝቅ ያለ ገቢ ላለው ወላጅ የልጅ እገዛ ገንዘብ መክፈል አለበት።

ልጆቼን ለመርዳት፡ ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚደረግ ግዜያዊ እርዳታ (የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ TANF) ተቀባይ ከሆንኩኝ፤ ይህንን ለልጆች እገዛ የሚደረገውን ገንዘብ ለማግኘት እችላለሁን ?

የልጅ ማሳደግያ እገዛ ገንዘብ (child support) እንዲከፈለኝ አዲስ ጉዳይ እንዴት ነው መጀመር የምችለው?

ፍርድ ቤት ውስጥ፤ የፍቺዬ ወይም የልጅ አሳዳጊነት ጉዳዬ በሚካሄድበት ወቅት፤ ለልጅ አሳዳጊ ስለሚሰጠው የገንዘብ እርዳታ ጉዳይ ማንሳት እችላለሁን?

የልጅ አሳዳጊ የገንዘብ እገዛ ጉዳይን እንደ አንድ የሲቪላዊ ጥበቃ ትእዛዝ **(Civil Protection Order (ሲ-ፒ-ኦ CPO)** አካል አድርጌ ለማቅረብ እችላለሁን?

በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት፤ በፍርድ ቤት ውስጥ የሚደረግ አዲስ  የአሳዳጊ የገንዘብ እገዛ ሂደት

በዚህ በኮቪድ-**19 (COVID-19)**እንዴት ነው የአሳዳጊነት የገንዘብ እርዳታን (child support) በሚመለከት አዲስ ጉዳይ ልጀምር የምችለው?

አዲስ የልጅ አሳዳጊነት የገንዘብ እገዛ እንዲደረግልኝ አቤቱታ በማቅረብ በኩል ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) እንዲረዳኝ ማመልከት እችላለሁን?

ጉዳዬ እንዲሰማ የተሰጠኝ የፍርድ ቤት ቀጥሮ፤ በዚህ በወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ ፍርድ ቤቶቹ በተዘጉባቸው ግዜያት ከሆነስ ምን ማድረግ አለብኝ?

መቼ ነው ፍርድ ቤቱ የሰጣቸውን ቀነ-ቀጠሮች ወደ ሌላ ቀን ማስተላለፍ የሚጀምረው?

ጉዳዬ የሚሰማበት የመጨረሻ ቀን ብሎ ፍርድ ቤት የሰጠኝን የመጨረሻ ቀን ጉዳይ (deadlines) ማከበር አለብኝን?

የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ በምን ላይ ተመርኩዞ እንደሚወሰን፣ እንዴት እንደሚከፈልና እንዴት እንደሚገኝ

በእንዴት አኳሃን ነው ለልጅ ማሳደግያ የሚሰጠው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ የሚታሰበው?

በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት፤ የአሳዳጊ የገንዘብ ክፍያ (Child Support) ጉዳይን በተመለከተ፤ አቤቱታ ለመጀመር አልቻልኩም። አቤቱታዬን ላቀርብ ላልቻልኩባቸው ግዜያት ክፍያ ላገኝ እችላለሁን?

ልጄ ከእኔ ጋር ነው የሚኖረው። እናቱ በቅርቡ በኮቪድ-19) (COVID-19) ምክንያት ስራዋን አጣች። ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ ከተሰጠ በኋላ የአሳዳጊነት ገንዘብ ትእዛዝ አሁንም ላገኝ እችላለሁን?

ለልጅ ማሳደግያ የሚሆን ገንዘብ በቀጥታ ከደሞዜ እየተቆረጠ ይሰጥ ነበር። በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ስራዬን አጣሁ። ለልጅ ማሳደግ ያ የምሰጠው ገንዘብ እንዳይቋረጥና እኔም ካለኝ ግዴታ ወደኋላ እንዳልል፤ ገንዘብም ሆነ ማንኛውንም ቁሳቁስ በቀጥታ ለእናቲቱ መላክ እችላለሁን?

የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ (Child support) ከአባትየው ደሞዝ እያተቆረጠ ነበር የሚሰጠኝ። አሁን በኮቪድ (COVID-19) በሽታ ምክንያት አባትዬው ከስራ ወጣ። እንዴት ነው የምከፈለው?

በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት፤ የልጅ ማሳደግያ ክፍያ የሚከፈል ከሆነ፤ መንግስት እንዴት አድርጎ ነው ለእኔ የሚልክልኝ?

የልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝን ስለማሻሻል

ልጆች ከእኔ ጋር የማይቀመጡ ወላጅ ነኝ። በቅርቡ ስራዬን አጥቻለሁ። ለልጅ ማሳደግያ የምከፍለውን ገንዘብ እንዴት ነው ዝቅ እንዲልልኝ የማደረገው?

ስራዎን ማጣት ወይም ከስራ መውጣትዎ' "በሁኔታዎች ላይ እንደመጣ እንደ አንድ ከተፍኛ ለውጥ" ሊታሰብ ይችላልን ?

በልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝ (child support order) ላይ ለውጥ ወይም መሻሻል እንዲደረግልኝ እንዴት ነው የምጠይቀው?

የልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝ እንዲሻሻልኝ ጥያቄ ካቀረብኩ ከሰንት ግዜ በኋላ ነው ጉዳዬ ፍርድ ቤት የሚሰማልኝ?

እንዲሻሻል ከታዘዘ በምን ቀን ነው ስራ ላይ የሚውለው?

የልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝን (Child Support Order) ስለማጠናከር

የልጄ እናት መክፈል የሚገባትን የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ አትከፍለኝም ያለችው። ምን ማድረግ እችላለሁ?

እንዴት አድርጌ ነው የተጣሰ የልጅ ማሳደግያ ትእዛዝን በተመለከተ አቤቱታ የማቀርበው?

በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) የቀውስ ግዜ ፤ ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) የልጅ ማሳደግያ ክፍያዎችን (child support) ለመሰብሰብ ምን እያደረገ ነው?

የልጅ አሳዳጊነት ተቆራጭ ገንዘብን በተመለከተ ያለው የህግ ድጋፍ

የህግ ድጋፍ እንዴት ለማግኘት እችላለሁኝ?

የልጅ አሳዳጊነት (CUSTODY)

ፍርድ ቤቱ ማን የአሳዳጊነት መብት እንደሚያገኝ እንዴት ይወስናል?

ፍርድ ቤቱ ለአንድ ወላጅ የብቸኛ የአካል አሳዳጊነት እና የብቸኛ የሕግ አሳዳጊነት መብት ሊፈርድበት የሚችለው ዕድል እንዴት ሊኖር ይችላል?

የአሳዳጊነት ጉዳይ መጀመር (Starting a Custody Case)

በዲስትሪክቱ ውስጥ የአሳዳጊነትን ክስ ለመጀመር የሚያስፈልገው ምንድነው?

ማነው ስለ ልጅ አሳዳጊነት ክስ ሊያቀርብ የሚችል?

የልጄ ህጋዊ አሳዳጊ እኔ መሆኔን ለማሳወቅ የፍርድ ቤት የአሳዳጊነት ትእዛዝ ያስፈልገኛልን?

ከሌላኛው ወላጅ የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ ለማግኘት፤ በፍርድ ቤት የተወሰነ የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዝ ያስፈልገኛልን?

አስቸኳይ የሆነ የአሳዳጊነት መብት እንዲሰጦት ስለመጠየቅ

አስቸኳይ የሆነ የአሳዳጊነት መብት እንዲሰጠኝ መቼ መጠየቅ አለብኝ?

በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት አስቸኳይ የአሳዳጊነት መብጥ ጥያቄ እንዴት ማቅረብ እችላለሁኝ?

የኮቪድ (COVID-19) ቀውስ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ ጉዳዬ በፍርድ ቤት ሲሰማ የሚያግዘኝ ህጋዊ ድጋፍ ላገኝ እችላለሁን ?

የአሳዳጊነት ትእዛዝን ማሻሻል

የአሳዳጊነት ትእዛዝ አንዴ ከጸደቀ በኋላ መቀየር ይቻላልን?

ፍርድ ቤቱ የአሳዳጊነትን ጉዳይ ለማሻሻል(Motion to Modify Custody) እንዴት ነው የሚወስነው?

ጉብኝት/ጥየቃ

ከፍርድ ቤት ምን ዓይነት የጉብኝት መብቶችን  ማግኘት እችላለሁ?

ወቅቱ የኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ወቅት በሆነበት በአሁኑ ግዜ፤ በፍርድ ቤት የተወሰነውን የልጆች ጉብኝት ትእዛዝ የግድ ማክበር አለብኝን?

በዚህ የኮቪድ (COVID-19) ወቅት፤ ታዛቢ ያለበት የጉብኝት ማእከሉ (Supervised Visitation Center) አሰራር ምን ይመስላል?

በዚህ በኮቪድ--19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ የተሰጠኝ የፍርድ ቤት ትእዛዝ፡ ልጆቹ ከሌላው ወላጅ ጋር የሚገናኙበት ታዛቢ ባለበት የጉብኝት ማእከል (Supervised Visitation Center) ነው ካለ ምን ማድረግ አለብኝ?

የአሳዳጊነት ትእዛዙ (custody order) ፤ በአንድ በተወሰነ ቦታ፤ ሶስተኛ አካል በታዛቢነት ባለበት ማእከል፤ አንዱ ወላጅ  ለሌላው ወላጅ ልጁን ለተወሰነ ግዜ የሚያስረክብ ከሆነና ወቅቱ የኮቪድ-19 የወረርሽኝ በሽታ ወቅት ከሆነ ምን ማድረግ አለብኝ?

አሳዳጊነትንና ጉብኝትን በተመለከተ የሚደረግ እርዳታ

የኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ የአሳዳጊነትን ጉዳይ በተመለከተ  የት ነው ህጋዊ እርዳታ ማግኘት የምችለው?

# ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support)

## ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support) ሲባል ምን ማለት ነው ?

ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support) ማለት አንዱ ወላጅ ለሌላኛው ወላጅ ወይም ሰው ለልጆቹ ማሳደግያ የሚሆን በቀጣይነት የሚከፍለው ገንዘብ ማለት ነው።

## ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support) ለማግኘት ብቁ የሚሆነው ማነው?

ልጆቹን በማሳደግ ላይ ያለው የልጅ አሳዳጊ፤ የልጅ ድጋፍ ለማግኘትና ለመቀበል ማመልከት ይችላል። አሳዳጊ የሚባለው፤ ልጆቹ ከእርሱ ወይም ከሷ ጋር የሚኖሩ ሲሆኑና አብዛኛውን ግዜያቸውን በዛው ስያሳልፉ ነው። አብዛኛውን ግዜ አሳዳጊ የሚባለው ወላጅ ነው፤ ይህም **አሳዳጊ ወላጅ** (custodial parent) ተብሎ ይጠራል። አንዳንዴ ደግሞ አሳዳጊ ወላጅ ሲባል፤ ልጁን የሚንከባከብ አክስት፣አጎት ወይም አያት ሊሆን ይችላል።

## ለአሳዳጊ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ (Child Support) የሚከፍለው ማነው?

ፍርድ ቤቱ፡ አንዱ ወገን የልጆቹ ወላጅ መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም **ከልጆቹ ጋር ግን የሚያሳልፈው ግዜ በጣም ጥቂት ከሆነ ፤ ከልጆች ጋር አብዛኛውን ግዜ ለሚያሳልፍ ወገን** የገንዘብ ድጋፉ እንዲከፍል ሊያዝ ይችላል።

- እናት፤ የልጁ የእውነት ወላጅ መሆንዋ ልጁ ሲወለድ ሊረጋገጥ ይችላል።
- የአባት ወላጅነት የሚረጋገጠው (1) አባት እኔ ነኝ ወላጅ ብሎ ራሱ ሲያረጋገጥ (2) ወላጅ መሆኑ ሲወሰንበት ወይም (3) በደምና በሌላም በሚደረግ ምርመራ ነው

## ለልጅ አሳዳጊ ድጋፍ ገንዘብ መስጠትን በተመለከተ፤ ፍርድቤቱ፤ የልጆቹ አሳዳጊ ማን መሆኑን የሚያረጋገጠው እንዴት ነው?

አሳዳጊ ተብሎ ለተሰየመ ሰው የአሳዳጊንት የገንዘብ እርዳታ ለመወሰን ተብሎ *የተደረገ ወቅታዊ የሆነ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ካለ*፤ ያ ትእዛዝ የልጆቹ አሳዳጊ ማን እንደሆነ ይወስናልማለት ነው።

የልጆችን የአሳዳጊነት ገንዘብ እገዛ በሚመለከት፡ *የፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሌለ፤* አብዛኛውን ግዜ ከልጆቹ ጋር የሚያሳልፍ አዋቂ ሰው ነው እንደ አሳዳጊ የሚቆጠረው። ልጆቹ ከአባታቸውም ጋር ይሁን ከእናታቸው ጋር የሚያሳልፉት ግዜ እኩል ከሆነ ከሁለቱ ወላጆች የበዛ ገቢ ያለው ወላጅ ዝቅ ያለ ገቢ ላለው ወላጅ የልጅ እገዛ ገንዘብ መክፈል አለበት።

## ልጆቼን ለመርዳት፡ ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚደረግ ግዜያዊ እርዳታ (የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ TANF) ተቀባይ ከሆንኩኝ፤ ይህንን ለልጆች እገዛ የሚደረገውን ገንዘብ ለማግኘት እችላለሁን ?

አንድ አሳዳጊ፤ በዲሲ ለተቸገሩ ቤተሰቦች ከመንግስት የሚሰጥ እርዳታ ገንዘብ የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ተቀባይ ከሆነ፤ የልጅ እገዛ ተብሎ የሚሰጠውን የገንዘብ እገዛ የመቀበል መብቱን መሰረዝና መብቱን ለመንግስት ማስረከብ አለበት። ከዛ በኋላ መንግስት በልጁ ወላጅ ላይ በፍርድ ቤት የልጅ እገዛ ጉዳይ በመጀመር በየቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) አማካይነት ለሌላኛው የከፈለውን የልጅ እገዛ ገንዘቡን ማስመለስ ይችላል።

በዲስትሪክቱ የልጅ እገዛ ማለፍያ መንገድ ፕሮግራም (District's Child Support Pass-Through Program) መሰረት የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ተቀባይ አሳዳጊዎች፤ በቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ለልጅ እገዛ ተብሎ የተከፈላቸው ገንዘብ እስኪገባደድ ድረስ፤ አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ በየወሩ ከሚከፍለው ገንዘብ $150' ውን መውሰድ ይችላሉ።

## የልጅ ማሳደግያ እገዛ ገንዘብ (child support) እንዲከፈለኝ አዲስ ጉዳይ እንዴት ነው መጀመር የምችለው?

እንደ ደንቡ ከሆነ፤ ለልጅ ማሳደግያ የሚሆን የገንዘብ እገዛ (child support) እንዲያገኙ አዲስ ጉዳይ ለመጀምር የሚያስችሉ ሁለት መንገዶች አሉ፤

- **የዲስትሪክቱ የልጅ ማሳደግያ እገዛ አገልግሎት ክፍል ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (Child Support Services Division, CSSD) አዲስ የልጅ ማሳደግያ እገዛ ጉዳይ እንዲጀምርሎት መጠየቅ።** ለዚህም ማመልከቻ application እንዲሞሉና አንዳንድ ዶኩመንቶችን በአካል ተገኝተው ለሴ-ኤስ-ኤሰ- ዲ (CSSD) ጽህፈት ቤት እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። ይሄው ጽህፈት ቤት በሚከተለው አድራሻ ላይ ይገኛል፤ 441 4ተኛው ጎዳና፤ ኖርትዌስት፤ የቤት ቁጥር 550 ሰሜን ዋሽንግተን ዲሲ (441 4th Street NW, Suite No 550 Washington D.C) ። ለችግረኛ ቤተሰቦች የሚደረርግ እርዳታ የቲ-ኤ-ኤን-ኤፍ (TANF) ወይም የሜዲኬድ (Medicaid) ጠቀሜታ ተቀባይ ካልሆኑ በስተቀረ፤ የ ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) እርዳታ ለመቀበል $5 እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ። አንዴ ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) ማመልከቻዎን ካጠናቀቀ በኋላ፤ የህግ ባለሞያዎቹ፤ የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ እንዲያገኙ ጥያቄውን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት (Petition for Child Support with the Superior Court) ያቀርባሉ። ከዚህም በኋላ የክሱን ቅጂ፤ የማሳደግያ ገንዘብ መክፈል ለሚገባው ወላጅ ይሰጣሉ።

- **የልጅ አሳዳጊ የገንዘብ እገዛ እንዲደረግሎት ራስዎም ወደ ከፍተኛው ፍርድ ቤት አዲስ ጥያቄዎን ማቅረብ ይችላሉ።** የሚረዳዎት ጠበቃ ከሌሎት፤ JM-570 የሚል ቁጥር በተጻፈበት ክፍል ውስጥ የሚገኘው የቤተሰብ ፍርድቤት ራስን በራስ የማገዝ ማእከል (The Family Court Self-Help Centerፎር) ሞልተው የሚያስገቡት ባዶ ፎርም ሊሰጦት ይችላል። ይህ ፎርምም የሚሞላው በክፍል JM-540 በሚገኘው በሴንትራል ኢንቴክ ማእከል (Central Intake Center) ውስጥ ነው። ለዚህም የሚከፍሉት ገንዘብ $80 ነው። ይህ ዋጋም እንዲነሳሎት ከፈለጉ ሌላ ካለክፍያ፤ ዋጋ ወይም ሴኩሪቲ የሚደረግ የልጅ አሳዳጊነት ክፍያ (Application to Proceed Without Prepayment of Fees, Costs and Security with your Petition for Child Support) የሚል ማመልከቻ ሞልተው ማቅረብ አለቦት።

አብዛኛውን ግዜ፤ ጉዳዩ በፍርድ ቤት በሚሰማበት በመጀመርያው ግዜ፤ የልጅ አሳዳጊነት ገንዘብ ይከፈለኝ ብለው ጥያቄ ባቀረቡ በ 45 ቀናት ውስጥ ነው።

ይህንኑን በተመለከተ፤ ወቅታዊ ለሆነ የሂደትም ሆነ የግዜ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ፤ በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት የልጅ የአሳዳጊነት የገንዘብ እርዳታ ሂደት (Child Support Proceedings During COVID-19) ጽሁፍ ይመልከቱ።

## ፍርድ ቤት ውስጥ፤ የፍቺዬ ወይም የልጅ አሳዳጊነት ጉዳዬ በሚካሄድበት ወቅት፤ ለልጅ አሳዳጊ ስለሚሰጠው የገንዘብ እርዳታ ጉዳይ ማንሳት እችላለሁን?

አዎን፡፡ የፍቺዎ ጉዳይና የልጅ አሳዳጊነት መብት ይሰጠኝ ብለው በፍርድ ቤት በቀርቡበት ወቅት፤ ስለዚሁ የአሳዳጊ የገንዘብ እርዳታ ጥያቄም በማናቸውም ግዜያት አንስተው መነጋገር ይችላሉ።

## የልጅ አሳዳጊ የገንዘብ እገዛ ጉዳይን እንደ አንድ የሲቪላዊ ጥበቃ ትእዛዝ (Civil Protection Order (ሲ-ፒ-ኦ CPO) አካል አድርጌ ለማቅረብ እችላለሁን?

አዎን። ግን ማንኛውም በሲ-ፒ-ኦ (CPO) በኩል የተገኘ የገንዘብ እርዳታ (የልጅ አሳዳጊነት የገንዘብ እገዛም ጭምር) የግዜ ገደብ አለው። ይሄውም አብዛኛውን ግዜ አንድ ዓመት ወይም ሁለት ዓመት ነው። ዓላማዎ የሲ-ፐ-ኦ ግዜው ካለቀም ብኋል የልጅ አሳዳጊነት ገንዘብ ማግኘትዎ እንዲቀጥል የሚፈልጉ ከሆነ፡ ጥያቄዎን በስ-ፒ-ኦ (CPO) በኩል አለማቅረብ ይበጅታል። ይህንኑን የልጅ አሳዳጊነት የገንዘብ እርዳታን በተመለከተ የተለየ ጥያቄ ለብቻው ማቅረብ የተሻለ ነው።

ሲ-ፒ-ኦ (CPO) ን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሊጋል ኤድ (Legal Aid) የቤተዘመድ ሁከትን በተመለከተ ያቀረበውን የጥያቄና መልስ ጽሁፍ ይመልከቱ።

# በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት፤ በፍርድ ቤት ውስጥ የሚደረግ አዲስ  የአሳዳጊ የገንዝብ እገዛ ሂደት

**<u>በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19)</u>እንዴት ነው የአሳዳጊነት የገንዘብ እርዳታን (child support) በሚመለከት አዲስ ጉዳይ ልጀምር የምችለው?**

በዚህ የኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ የላይኛው ፍርድ ቤት፤ የልጅ የአሳዳጊ ገንዘብ ጉዳዮችን በሙሉ በስልክ ወይም በቪዲዮ በሚደረጉ ግንኙነቶች ወይም ስብሰባዎች ይመለከታል። አንድ ጉዳይ፤ በስልክ ወይም በቪዲዮ እንዲሰማ አዲስ ቀነ-ቀጠሮ ሲሰጠው፤ የላይኛው ፍርድ ቤት፤ ባለ ጉዳይ እንዴት በዚህ ዓይነቱ ስብሰባ እንደሚሳተፍ የሚያስረዳ አዲስ መረጃ ይልካል።

የአሳዳጊነት የገንዘብ እገዛን (Child Support) በሚመለከት፤ የላይኛው ፍርድ ቤት፤ <u>በግል አሳዳጊዎች</u> ወይም በሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ(CSSD የገንዘብ እርዳታ (TANF) በሚያገኙ አማካኝነት የሚቀርቡ አዲስ አቤቱታዎችን ይቀበላል።

- የአሳዳጊነት የገንዘብ እገዛን (Child Support) በሚመለከት ከሰኞ እስከ ዓርብ፤ ከጥዋቱ 8:30 እስከ ከሰዓት በኋላ 5:00 ሰዓት ድርስ ክፍት ወደሆነውና በዲሲ ውስጥ ወደሚገኘው የላይኛው ፍርድ ቤት፤ ክፍል JM-540 በአካል በመሄድ ማመልከት ይችላሉ። የሚከፈል የምዝገባ ክፍያ ካለ ደግሞ እንዲሁ በአካል ተገኝተው ክፍያው እንዲነሳሎ ማመልከት ይችላሉ። ይህ ጥያቄ ክፍያ ላለመክፈል የሚደረግ ማመልከቻ (Application to Proceed Without Payment of Costs, Fees or Security) በመባል ይታወቃል።
- ይህንን ክፍያ ላለመክፈል ከፈለጉ ወደ  FamilyCourtCIC@dcsc.gov ኢሜል በመጻፍ ማመልከት ይችላሉ

- ይህንን ማመልከቻ ለመሙላት ብቁ ካልሆኑ ወይም ይህንን አቤቱታ ማቅረብ የማይፈልጉ ከሆነ፤ የአሳዳጊነት ገንዘብ እንዲሰጥዎት የምታቀርቡት አቤቱታ በ ኬዝፋይልኤክስፕሬስ (CaseFileXpress) ማመልከት ይችላሉ፤ በዚህም የመመዝገብያ $80 እንዲከፍሉ

ይጠየቃሉ። አዲስ የኬዝፋይልኤክስፕሬስ (CaseFileXpress) ፋይል ለመክፈትም አሁንም ከቤተሰብ ፍርድ ቤት **Family Court** ጋር መገናኘት አለቦት።

## አዲስ የልጅ አሳዳጊነት የገንዘብ እገዛ እንዲደረግልኝ አቤቱታ በማቅረብ በኩል ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) እንዲረዳኝ ማመልከት እችላለሁን?

አዎን። የሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) ሰራተኞች ሊያግዞት ይችላሉ።

የሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) መስርያ ቤቶች በአሁኑ ወቅት ህዝብ በአካል ለመቀበል ዝግ ናቸው። ግን በስልክ ቁጥር (202) 442-9900 ከሰኞ እስከ ዓርብ፤ ከጥዋቱ 8:15 እስከ 4:45 ከሰዓት በኋላ በመደወል ወይም በኢሜል cssdcustomerservice@dc.gov በመጻፍ ከሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) ጋር ለመገናኘት ይችላሉ። በአሁኑ ወቅት ሰራተኞች ሁሉ በስልክ ስለሚሰሩ ምናልባት ለጥሪዎ ወድያውኑ መልስ እስኪያገኙ ድረስ ግዜ ይፈጅ ይሆናል።

## ጉዳዬ እንዲሰማ የተሰጠኝ የፍርድ ቤት ቀጥሮ፤ በዚህ በወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ ፍርድ ቤቶቹ በተዘጉባቸው ግዜያት ከሆነስ ምን ማድረግ አለብኝ?

በዚህን ጊዜ፣ ፍርድ ቤቱ አዲስ የፍርድ ቤት ቀጠሮዎችን ልኳል። እነዚህ የቪድዮ ቀጠሮ ማስታወሻዎች ካልደረሶት ወደ ፍርድ ቤቱ ይደውሉ።

## መቼ ነው ፍርድ ቤቱ የሰጣቸውን ቀነ-ቀጠሮች ወደ ሌላ ቀን ማስተላለፍ የሚጀምረው?

የአሳዳጊ ገንዘብ የማግኘት አዲስ አቤቱታዎችን በተመለከተ፤ ሲያመለክቱ፤ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዮ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ይሰጦታል። ግን ጉዳዮ በ45 ቀናት ውስጥ ይሰማል የሚለው በአሁኑ ግዜ የሚሰራ አይመስልም ምክንያቱም ቀደም ሲሉ የቀረቡ አቤቱትታዎች በቀደምትነት መሰማት ስላለባቸው።

### ጉዳዬ የሚሰማበት የመጨረሻ ቀን ብሎ ፍርድ ቤት የሰጠኝን የመጨረሻ ቀን ጉዳይ (deadlines) ማከበር አለብኝን?

አዎን። ማክበር አለቦት። ስለዚሁ ጉዳይ ከጠበቃዎ ጋር ይነጋገሩ።

# የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ በምን ላይ ተመርኩዞ እንደሚወሰን፣ እንዴት እንደሚከፈልና እንዴት እንደሚገኝ

### በእንዴት አኳሃን ነው ለልጅ ማሳደግያ የሚሰጠው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ የሚታሰበው?

አብዛኛውን ግዜ ዳኞች፣ የልጅ የማሳደግያ ገንዘብ ምን ያህል መሆን እንዳለበት ሲያጠኑ የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ መመርያዎችን (Child Support Guideline) (D.C. Code § 16-916.01) ይከተላሉ። አንዳንዶቹ መመርያዎች የወላጆቹ ገቢ ምን ያህል ነው፡ የገንዘብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የልጆች ቁጥር ምን ያህል ናቸው የሚለውና ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር ምን ያህል ግዜ ነው የሚያሳልፉት የሚቀር ጥያቄዎች ግምት ውስጥ ያስገባሉ። ሌላ መመርያዎቹ ግምት ውስጥ የሚያስገቡት፤ የህጻናት መዋያዎች እንዲሁም የ ሕክምና ኢንሹራንስ ወይም የህክምና ወጪያቸው ምን ያህል ነው የሚሉ ናቸው።

ለልጆች ማሳደግያ ገንዘብ ምን ያህል መሆን እንዳለበት ለማወቅ ይህንን የሚቆጥር ቆጣሪን ኦንላይን http://cssd.dc.gov/service/calculate-child-supportpayments በመግባት ማየት ይቻላል።

አብዛኛውን ግዜ ዳኞች በመመርያው የተጻፈውን ስሌት ይጠቀማሉ ይሁንና ለውሳኔያቸው በቂ ምክንያት ካቀረቡ ሌል የገንዘብ ልክ ለማዘዝ ይችላሉ። በተጨማሪም ሁለቱ ወላጆች፤ ይሄን ያህል መክፈል አለበት ብለው ከተስማሙ፤ ዳኛው ሊያጽድቅላቸው ይችላል።

## በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት፤ የአሳዳጊ የገንዝብ ክፍያ (Child Support) ጉዳይን በተመለከተ፤ አቤቱታ ለመጀመር አልቻልኩም። አቤቱታዬን ላቀርብ ላልቻልኩባቸው ግዜያት ክፍያ ላገኝ እችላለሁን?

አዎን። ቀጣይ የሆነ የአሳዳጊነት ገንዘብ እንዲሰጦት ከመጠቅዎ በተጨማሪ ጉዳዮን ከማቅረቦ እስከ 24 ወራት በፊት ክፍያው ወደኋላ ሂዶ እንዲሰጦት መጠየቅ ይችላሉ።

## ልጇ ከእኔ ጋር ነው የሚኖረው። እናቱ በቅርቡ በኮቪድ-19) (COVID-19) ምክንያት ስራዋን አጣች። ጉዳዩ እንዲሰማ ቀጠሮ ከተሰጠ በኋላ የአሳዳጊነት ገንዘብ ትእዛዝ አሁንም ላገኝ እችላለሁን?

ምናልባት አዎን። አብዛኛውን ግዜ፤ ምናልባት ገንዘብ የሚሰጠው ወላጅ ከስራ ከወጣ ተብሎ በአነስተኛ መጠን የተወሰነ የገንዝበ ክፍያ የሚደነገግ አለ። ፍርድ ቤቱ፤ ከስራ የወጣው ወላጅ ወይም የስራ ሰዓቱ የጎደለበት ወላጅ አነስተኛውን ገንዘብ ለመክፈል ይችላል ብሎ ካመነ፤ በወር $75 እንዲከፍል ያዛል። ከፋዩ ወላጅ ደግሞ $75 ለመክፈል እንደማይችል ማረጋገጫ በማቅረብ፤ የሚከፍለው ገንዘብ ከዛ በታች እንዲሆንለት ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላል።

በተጨማሪም፤ ፍርድ ቤቱ  ልጆቹ ከሱ ጋር የሌሉ ግን የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ ልጆቹን ለያዘው ወገን መክፈል ያለበት ወላጅ፤ ሙሉ ክፍያ የሚከፈልበት ስራ እስኪያገኝ ድረስ፤ ስራ ለማግኘት ቢያንስ በሳምንት ውስጥ አስር የስራ መፈለግ ሙከራዎችን በመውሰድ፤ ስራ አግኝቶ ለልጆቹ ማሳደግያ የሚከፍለውን ገንዘብ መክፈሉን እንዲቀጥል ያዛል።

## ለልጅ ማሳደግያ የሚሆን ገንዘብ በቀጥታ ከደሞዜ እየተቆረጠ ይሰጥ ነበር። በኮቪድ-19 (COVID-19) ምክንያት ስራዬን አጣሁ። ለልጅ ማሳደግ ያ የምሰጠው ገንዘብ እንዳይቋረጥና እኔም ካለኝ ግዴታ ወደኋላ እንዳልል፤ ገንዘብም ሆነ ማንኛውንም ቁሳቁስ በቀጥታ ለእናቲቱ መላክ እችላለሁን?

አትችሉም። ከደሞዞ በቀጥታ ተቆርጦ ለሌላው ወገን መስጠት የማይቻል ከሆነ፤ የልጅ ማሳደግያ ክፍያውን (child support) ወደ CSSD’s website ወይም ወደ ዲሲ D.C Child Support Clearinghouse በመግባት ሊከፍሉ ይችላሉ ወይም በጥሬ ገንዘብ በከተማው ውስጥ ወደ ተወሰኑ ሱቆች paying in cash at certain retail locations በመሄድ ሊከፍሉ ይችላሉ። እነኚህ ዓይነቶቹ አከፋፈሎች ኮቪድ-19 (COVID-19) ባስከተለው ቀውስ አልተነኩም። ስለዚህ ከፍለዋል የሚባሉት በእነዚህ መንገዶች በአንዱ ሲከፍሉ ነው። ራስዎ በግሎ፤ ልጆችዎንን ለያዘ አሳዳጊ በገንዘብም ይሁን በቆሳቁስ መልክ የሚያደርጉት ክፍያ እንደ ስጦታ ነው የሚቆጠርሎት እንጂ የልጅ ማሳደግያ ክፍያ ተብሎ አይታሰብሎትም።

## የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ (Child support) ከአባትየው ደሞዝ እያተቆረጠ ነበር የሚሰጠኝ። አሁን በኮቪድ (COVID-19) በሽታ ምክንያት አባትዬው ከስራ ወጣ። እንዴት ነው የምከፈለው?

በቅርቡ ከስራ የወጣ፤ ልጆቹ ከሱ ጋር የሌሉ ወላጅ፤ ከስራ ስለወጣ ከስራ የመውጣት ክፍያ (unemployment insurance) እንዲከፈለው ካመለከትና ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ፤ የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ ከዛው ከሚያገኘው ገንዘብ እየተቆረጠ ለሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) በቀጥታ ይላካል።

ልጆቹ ከሱ ጋር የሌሉ የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ ይከፍል የነበረው ወላጅ ስራውን ቢያጣ ግን የስራ መውጣት ክፍያ (unemployment insurance) የማይከፈለው ከሆነ ቀደም ሲሉ ከተጠቀሱት መንገዶች በአንዱ፤ መክፈል የሚጠበቅበትን ክፍያ መክፈል አለበት።

### በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት፤ የልጅ ማሳደግያ ክፍያ የሚከፈል ከሆነ፤ መንግስት እንዴት አድርጎ ነው ለእኔ የሚልክልኝ?

የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ (child support) በቀጥታ ወደ ባንኮ እንዲገባሎት ወይም በቀጥታ ልጅ ማሳደግያ ገንዘብ ዴቢት ካርዶ ውስጥ እንዲገባሎት ማድረግ ይችላሉ። ከእነዚህ ሁለቱ አማራጮች ማንኛውንም የማይመርጡ ከሆነ ደግሞ ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) ገንዘቡን በወረቀት ቼክ ወደ ቤትዎ ይልክሎታል።

ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) እንደገለጸው የልጅ ማሳደግያ ክፍያዎች (child support payments) እንደተለመደው ወደ ሚመለከታቸው እየተላኩ ነው።እስኪያገኙት ድረስ የሚቆይቦት ከሆነዘወትር ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 8:15 እስከ 4:45፤ በስልክ ቁጥር (202) 442-9900 ወደ ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) በመደወል ወይም በኢሜል cssdcustomerservice@dc.gov በመጻፍ ለምን እነደሚቆይቦት ይጠይቁ ። በአሁኑ ወቅት የ ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) ሰራተኞች በስልክ ብቻ ስለሚሰሩ ከእነሱ ጋር ለመነጋገር መስመሩን ለማግኘት ግዜ ሊወስድ ይችላል።

## የልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝን ስለማሻሻል

### ልጆች ከእኔ ጋር የማይቀመጡ ወላጅ ነኝ። በቅርቡ ስራዬን አጥቻለሁ። ለልጅ ማሳደግያ የምከፍለውን ገንዘብ እንዴት ነው ዝቅ እንዲልልኝ የማደረገው?

የልጆቹን ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ሊቀይር የሚችል ነገር ሲያጋጥም ወይም በመክፈል ችሎታዎ ላይ አንዳች ለውጥ ሲመጣ፤ ፍርድ ቤቱ፤ በልጅ ማሳደግያ ክፍያ ላይ ያጸደቀውን ዘላቂ ትእዛዝ እንድያሻሽልሎ ፍርድቤቱን መጠየቅ ይችላሉ።

ይህም ሲባል *በሁኔታዎች ላይ ከፍተኛ ለውጥ እንደመጣ* ማረጋገጫ በማቅረብ ማስረዳት አለቦት። ሁኔታዎች ባይቀያየሩም በየሶስት ዓመቱ የሚከፍሉት የልጅ ማሳደግያ ክፍያ እንደገና እንዲታይሎ ወይም በትእዛዙ ላይ አንዳች ለውጥ እንዲደረግሎ መጠየቅ ይችላሉ።

## ስራዎን ማጣት ወይም ከስራ መውጣትዎ “በሁኔታዎች ላይ እንደመጣ እንደ አንድ ከተፍኛ ለውጥ” ሊታሰብ ይችላልን ?

አዎን። ከኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ጋር በተያያዘ መልኩ ከስራ መውጣትና የደሞዝ መጉደል በልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝ (child support order) ላይ መሻሻል የሚያስፈገው እንደ አንድ “በሁኔታዎች ላይ እንደመጣ ከፍተኛ ለውጥ ” ሊታሰብ ይችላል።

## በልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝ (child support order) ላይ ለውጥ ወይም መሻሻል እንዲደረግልኝ እንዴት ነው የምጠይቀው?

ፍርድ ቤቱ በልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝ (child support order) ላይ ለውጥ እንዲያደርግ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው Motion to Modify Child Support with the Court የተባለውን ሞልቶ ለፍርድቤቱ ማቅረብ አለበት። ወደ ራስን በራስ የማገዝ የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማእከል (Family Court Self-Help Center) በስልክ ቁጥር 202-879-0096 በመደወል ጉዳያቸውን የማቅረብና አስፈላጊውን ፎርም የመሙላት እገዛ በቨርቹዋል ያገኛሉ።

አቤቱታዎን በቀጥታ በኢሜል ለፍርድ ቤቱ ማቅረብም ይችላሉ። ኦንላይን ወደ Motion to Modify Child Support ገብተው ባዶ ፎርሙን አትመው ያውጡና ከሞሉት በኋላ በኢሜል አድራሻ **FamilyCourtCIC@dcsc.gov** ይላኩ።

ፍርድ ቤቱ የሚከፈል ዋጋ እንዲነሳላቸው የሚጠየቁ ያልተወከሉ አመልካቾችን ማመልከቻ ብቻ ነው የሚቀበለው። ክፍያ እንዲነሳሎ፤ ይህንን *ምንም ዋጋ ሳይከፈል የማመልከቻውን ጉዳይ መቀጠል* ( Application to Proceed Without Prepayment of Fees, Costs or Security) የሚል ማመልከቻ መሙላት አለበት።

በተጨማሪም በ ዲሲ ላይኛው ፍርድ ቤት ውስጥ በ ክፍል JM-540 ወደሚገኘው የቤተሰብ ፍርድ ቤት ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ ጥዋቱ 8:30ሰዓት እስከ ከሰዓት በኋላ 5:00 ሰዓት በአካል ሂደው ሊያመለክቱ ይችላሉ።

## የልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝ እንዲሻሻልኝ ጥያቄ ካቀረብኩ ከሰንት ግዜ በኋላ ነው ጉዳዬ ፍርድ ቤት የሚሰማልኝ?

በ COVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት፣ ፍርድ ቤቱ ጥቂት ችሎቶችን ብቻ ይመለከታል።በጣም የተጠራቀሙ ክሶች በመኖራቸው የተነሳ፣ ለስልክ ወይም ለቪዲዮ ሰሚ ችሎት አዲስ ቀጠሮ እስከሚቆረጥልዎት ድረስ በጣም ብዙ ወራትን ሊወስድ ይችላል።

በዚህ በኮቪድ (COVID-19) ቀውስ ምክንያትም፤ ፍርድ ቤቱ፤ አዲስ የገቡ፤ የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ ትአዛዞችን የማሻሻል ጉዳዮችን መቸ መስማት እንደሚጀምር የታወቀ ነገር የለም።

## እንዲሻሻል ከታዘዘ በምን ቀን ነው ስራ ላይ የሚውለው?

ፍርድ ቤቱ፤ የልጅ ማሳደግያ ክፍያን በተመለከተ፤ መሻሻል እንዲደረግ ከተስማማ፤ ተእዛዙ እንዲሻሻል ማመልከቻ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ለውጡ እንዲደረግ ሊወስን ይችላል።

- ***ለምሳሌ*** *፤ ትእዛዙ እንዲሻሻል ጥር 1 ቀን ላይ ጥያቄ ቢቀርብና ፍርድ ቤቱ ግን እስከ መጋቢት 1 ቀን ድረስ ገና ውሳኔ ያልሰጠ ከሆነ፤ ውሳኔውን ሲያሳልፍ የገንዘብ ክፍያው ለውጥ ወደኋላ ተመልሶ ጥር አንድ ቀን ላይ እንዲጀምር ሊያደረግ ይችላል።*

የክፍያውን መሻሻል፤ የመሻሻል ጥያቄው ለፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት እንዲሆን ማድረግ በመንግስት ህግ መሰረት አጥብቆ የተከለከለ ነው። <u>ስለዚህ ስራዎን እንዳጡ ወድያውኑ ለፍርድ ቤት ማመልከት እጅግ አስፈላጊ ነው።</u>

- ***ለምሳሌ፤ በኮቪድ**-19 (COVID-19) ምክንያት፤ ልጆቹ ከሱ ጋር የሌሉ ወላጅ፤ ስራውን ያጣው መጋቢት 20 ከሆነ፤ ግን የሚከፍለው የልጅ ማሳደግያ ክፍያ እንዲሻሻልለት እስከ ግንቦት 1 ድረስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ካላቀረበ፤ ፍርድ ቤቱ ክፍያው እንዲሻሻል ሲወሰን፤ ከግንቦት 1ቀን ጀምሮ ትእዛዙ እንዲሻሻል ብሎ ነው ውሳኔ ሊያሳልፍ የሚችለው እንጂ ላልተጠየቀበት ግዚያት ትእዛዝ ሊሰጥ አይችልም። ስለዚህ ከፋይ ወላጅ፤ ከ መጋቢት 20 እስከ ግንቦት 1 ቀን ላሉት ግዜያት፤ ስራ ከመውጣቱ በፊት የተወሰነበትን ከፍተኛ ክፍያ መክፈል አለበት።*

የማእከላዊው መንግስትም ይሁን የዲስትሪክቱ አስተዳደር፤ የልጅ ማሳደግያ ክፍያ የሚከፈልበትን የመጨረሻ ቀን (deadlines) ለማሻሻል ዕቅድ እንዳለው ያወጀው ምንም ነገር የለም።

# የልጅ ማሳደግያ ክፍያ ትእዛዝን (Child Support Order) ስለማጠናከር

## የልጄ እናት መክፈል የሚገባትን የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ አትከፍለኝም ያለችው። ምን ማድረግ እችላለሁ?

ልጆቹ ከሱጋር የሌሉና ለሌላኛው ወገን የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ የሚከፍል ወላጅ፤ በፍርድ ቤት የታዘዘበትን የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ (Child Support) ለመክፈል አሻፈረኝ ካለ፤ ተቀባዩ፤ [Motion for Contempt of Child Support Order] የተባለ ትእዛዝ ሞልቶ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይቻላል። ይህ ትእዛዝ፤ ልጆች ከእርሱ ጋር የሌሉ ወላጅ፤ በፍርድ ቤት የታዘዘውን ገንዘብ አልከፍልም በማለቱ ገንዘቡን በመጠኑም ቢሆን እስኪከፍል ድረስ በእስር እንዲቆይ የሚያደርግ ትእዛዝ ነው።

ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) ቤተሰቦች የሚገባቸውን ገንዘብ እንዲያገኙ ለማገዝ፤ ሌሎች ትእዛዝ ማጠናከርያ መንገዶችም አሉት።

## እንዴት አድርጌ ነው የተጣሰ የልጅ ማሳደግያ ትእዛዝን በተመለከተ አቤቱታ የማቀርበው?

የልጅ ማሳደግያ የክፍያ ትምእዛዝ ከተጣሰቦት ወደዚሁ ከፍተኛ ፍርድ ክፍል JM-540 ወደ ሚገኘው የቤተሰብ ፍርድ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ ጥዋቱ 8:30 ሰዓት እስከ ከሰዓት በኋላ 5:00 ሰዓት በአካል ሂደው ሊያመለከቱ ይችላሉ።Application to Proceed Without Prepayment of Fees, Costs or Securitys የሚባለውን ቢያመለከቱም ባያመለክቱም በአካል ሂደው ማመልከት ይችላሉ።

ኦንላይን ገብተው ባዶ የ Motion for Contempt ፎርም ሊያገኙ ይችላሉ። ይህን ፎርም አትመው በማውጣት ከሞሉት በኋላ በኢሜል FamilyCourtCIC@dcsc.gov ወደ ቤተሰብ ፍርድ ቤት ይላኩ። ይላኩ። ወደ ቤተሰብ ፍርድ ቤት (Family Court's Central Intake Center) ይላኩት። ፍርድ ቤቱ በኢሜል አቤቱታዎችን የሚቀበለው Application to Proceed Without Prepayment of Fees, Costs or Securitys ከሚባለው፤ ክፍያ ላለመክፈል ፍቃድ ካሎት ወይም የተፈቀደሎትን ወረቀት ከአቤቱታዎ ጋር አያይዘው ሲልኩ ብቻ ነው።

ይህንን ማመልከቻ ለሞምላት ብቁ ካልሆኑ ወይም ፎርሙን ለመሙላት እቅድ ከሌሎት፤ በ ኬዝፋይሌክስፕሬስ CaseFileXpress) አማካኝነት ሊሞሉ የማመልከቻ ክፍያውን መክፈል ይችላሉ።

## በዚህ በኮቪድ-19 (COVID-19) የቀውስ ግዜ ፤ ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ (CSSD) የልጅ ማሳደግያ ክፍያዎችን (child support) ለመሰብሰብ ምን እያደረገ ነው?

በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ፤ ሲ-ኤስ-ኤስ-ዲ(CSSD) ፤ Motions for Contempt የተባለውን ክስ በመመስረት የሚያግዛቸውን ቤተሰቦች በመወከል ፤ ክፍያዎቻቸውን የማይከፍሉ ወላጆችን የመንጃ ፈቃዳቸው እንዲታገድ ወደ ሞቶር መኪናዎች ክፍል (Department of Motor Vehicles) ሊመራቸው ይችላል፤ ወይም የልጅ አሳዳጊነት ክፍያ የማይከፍል ወላጅን የባንክ ሂሳቡ እንዲያዝ ማድረግ ይችላል።

# የልጅ አሳዳጊነት ተቆራጭ ገንዘብን በተመለከተ ያለው የህግ ድጋፍ

### የህግ ድጋፍ እንዴት ለማግኘት እችላለሁኝ?

የእርስዎን የልጅ ማሳደጊያ ድጋፍ በተመለከተ፤ ምክር እና ድጋፍ ለመጠየቅ፤ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ሌጋል ኤድ ሶሻይቲን (Legal Aid Society) ማግኘት ይችላሉ። ምንም እንኳን የሌጋል ኤድ ሶሻይቲ ቢሮዎች ቢዘጉም፣ ጠበቃዎቻችን በስልክ እየሰሩ ነው እና አዲስ ደንበኞችን ለማነጋገር ይገኛሉ። የእኛን አገልግሎት ለማግኘት በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 በመደወል ወይም [አንላይን በመግባት](#) ማመልከት ይችላሉ።

እንደ አንድ የፍቺ ወይም የአሳዳጊነት ጉዳይ አካል የሆኑ የልጅ ማሳደጊያ ድጋፍ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ ለማግኘት፣ በስልክ ቁጥር (202) 844-5428 በመደወል የቤተሰብ ሕግ ድጋፍ ሰጪ ኔትወርክ (Family Law Assistance Network) ("FLAN")፤ የዲሲ ጠበቆች ማህበር ነፃ አገልግሎት ሰጪ ማእከል (D.C. Bar Pro Bono Center) ፣ ሌጋል ኤድ (Legal Aid) እና የዲሲን ተመጣጣኝ የህግ ትካልን( D.C. Affordable Law Firm) ማግኘት ይችላሉ።

# የልጅ አሳዳጊነት (CUSTODY)

# የልጅ አሳዳጊነት ምን ማለት ነው?

የልጅ አሳዳጊነት ማለት ወላጆች ልጆቻቸው 18 ዓመት እሰኪሞላቸው ድረስ የመንከባከብና ውሳኔ የመወሰን የሚያስችላቸው የህግ ሃላፊነት እና መብት ነው። ሁለት ዓይነት መብቶች አሉ- የሕግ አሳዳጊነት እና የአካል አሳዳጊነት።

- የሕግ አሳዳጊነት (Legal custody) ልክ እንደ ትምህርት፣ ጤና፣ ኣና ሃይማኖት የመሳሰሉ ጉዳዮችን በተመለከተ ለልጃቸው ዋና ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ የሚያስችል የወላጆች አቅም ነው። የሕግ አሳዳጊነት መብት ለብቻ ወይም በጋራ ሁኔታ ሊሰጥ ይችላል።

○ ፍርድ ቤቱ ለጥንዶቹ የጋራ ሕጋዊ የማሳደግ መብት እንዲኖራቸው የሚበይን ከሆነ፣ ልጁን በተመለከተ ማንኛውም አስፈላጊ ውሳኔዎችን በተመለከተ እርስበእርስ መነጋገር እና ማንኛውም አንገብጋቢ ውሳኔዎች ላይ መስማማት አለባቸው። አንዳንድ ሁኔታዎች ላይ፣ ፍርድ ቤቱ የጋራ ሕጋዊ አሳዳጊነት መብት ሊሰጥ እና ለአንደኛው ወላጅ የመጨረሻውን ውሳኔ የመወሰን ስልጣን ሊሰጥ ይችላል፣ ይሄ ማለት ወላጆቹ አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ መመካከር አለባቸው፣ ነገር ግብ የማይስማሙ ከሆነ፣ የመጨረሻውን ውሳኔ የማሳለፍ ስልጣን ያለው ወላጅ የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል ማለት ነው።

○ ፍርድ ቤት ለአንደኛው ወላጅ ብቻ የአሳዳጊነት መብት የሰጠ ከሆነ፣ አንደኛው ወላጅ ሌላኛውን ወላጅ ማነጋገር ሳያስፈልገው ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላል ማለት ነው።

- የአካል አሳዳጊነት (Physical custody) ማለት ልጁ የት እንደሚኖር እና ጊዜውን የት እንደሚያሰልፍ የሚከታተል ነው። የአካል አሳዳጊነት በአንድ ወላጅ ብቻ ወይም በጋራ ሁኔታ ሊወሰን ይችላል።

○ የጋራ የአካል አሳዳጊነትን መብትን ፍርድ ቤቱ የሚወስን ከሆነ፣ ልጅ/ልጅቷ ከኣያንዳንዱ ወላጅ ጋር አንዳንድ ጊዜ ያሳልፋሉ ማለት ነው። የጋራ የአካል አሳዳጊነት ማለት ልጁ/ልጅቷ ከእያንዳንዱ ወላጅ ጋር እኩል ሰዓት ያሳልፋሉ ማለት አይደለም።

○ ፍርድ ቤቱ ለአንደኛው ወላጅ ብቻ የአካል አሳዳጊነት መብት ከሰጠ፣ ልጁ ከአንደኛው ወላጅ ጋር ብቻ ሙሉ ለሙሉ ይኖራል። በተጨማሪም፣ ፍርድ ቤቱ ልጁን/ልጅቷን መጎብኘት እንዲችሉ የተወሰነ ጊዜ ለአንደኛው ወላጅ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

## ፍርድ ቤቱ ማን የአሳዳጊነት መብት እንደሚያገኝ እንዴት ይወስናል?

ዳኛው ወይም ፍርድ ቤቱ፤ ከሁለቱም ወገኖች ከሰማ በኋላ፣ የልጁን/ልጅቷን ጥቅም በበለጠ ሊጠብቅ ይችላል በሚል ውሳኔ ላይ ለመድረስ፤ አስራ ሰባት መስፈርቶችን (“ምርጥ ጥቅምን የሚያስጠብቁ መስፈርቶች “best interest factors” ተብለው የሚጠሩትን) ይመለከታል።

### ፍርድ ቤቱ ለአንድ ወላጅ የብቸኛ የአካል አሳዳጊነት እና የብቸኛ የሕግ አሳዳጊነት መብት ሊፈርድበት የሚችለው ዕድል እንዴት ሊኖር ይችላል?

አብዛናዎቹ ክሶች ላይ፣ ፍርድ ቤቱ ለወላጆቹ የጋራ የአካል አሳዳጊነት እና የሕግ አሳዳጊነት መብት ይሰጣል። የጋራ አሳዳጊነት መብት ለልጁ ምርጥ ጥቅም ይሰጣል የሚል በክርክር ሊሻር የሚቻል አመለካከት የዲስትሪክቱ ሕግ ስለሚያካትት ነው።

አንደኛው ወላጅ በሌላኛው ወላጅ ላይ የአካል ጥቃት እንዳደረሰ፣ እንደበደለ፣ ወይም ልጆቹን ችላ እንዳለ፣ ወይም የወላጅ ማገት ስራ እንደሰራ የሚያሳይ ማስረጃ ካቀረበለት፣ ፍርድ ቤቱ የጋራ አሳዳጊነት መብት ለልጁ ጥቅም ይሰጣል ብሎ ፍርድ ቤቱ አያምንም። ከዚህ ይልቅ፣ ጥቃት ለማያደርሰው ወላጅ የብቸኛ አሳዳጊነት መብትን መስጠት ለልጁ ምርጥ ይሆናል ብሎ ያስባል።

# የአሳዳጊነት ጉዳይ መጀመር (Starting a Custody Case)

### በዲስትሪክቱ ውስጥ የአሳዳጊነትን ክስ ለመጀመር የሚያስፈልገው ምንድነው?

በአጠቃላይ፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ልጆች ጉዳዩ ከመነሳቱ በፊት፤ በዲስትሪክቱ ውስጥ ቢያንስ ለ ስድስት ተከታታይ ወራት መቀመጥ አለባቸው።

### ማነው ስለ ልጅ አሳዳጊነት ክስ ሊያቀርብ የሚችል?

ልጅ ከእነሱ ጋር ይኑር አይኑር፤ ከሁለቱ ወላጆች ማንኛውም ክስ ሊያቀርብ ይችላል።

በተጨማሪም፤ ከወላጆች ውጪ፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ አያቶች፣ አጎቶች፣ አክስቶች የልጅ አሳዳጊነት መብት ለማግኘት ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ። እነኚህ ሶስተኛ አካሎች ለልጅ አሳዳጊነት ጥያቄ ሊያቀርቡ የሚችሉት፤

- ላለፉት ሶስት ዓመታት ለልጆቹ እንክብካቤ ስያደርግ የቆየ ወላጅ ስምምነቱን ሲሰጣቸው

- ካለፉት 6 ወራት ውስጥ ቢያንስ ለ4 ወራት ከልጁ ጋር የኖሩና እንክብካቤ ሲያደርጉለት የቆዩ ሲሆኑ

- በአሁኑ ወቅት ከልጁ ጋር በመኖር ላይ ያሉና የልጅ አሳዳጊነት መብት ካልተሰጣቸው፤ ልጁ ጉዳት ላይ የሚወድቅ ሲሆን

ሶስተኛው አካል ከእነዚህ ከተጠቀሱት ውስጥ ቢያንስ አንዱን የማያሟሉ ከሆነ፡ ልጁን ለማሳደግ ማመልከቻ ማቅረብ አይችሉም።

## የልጄ ህጋዊ አሳዳጊ እኔ መሆኔን ለማሳወቅ የፍርድ ቤት የአሳዳጊነት ትእዛዝ ያስፈልገኛልን?

አያስፈልጎትም። ልጅዎን ትምህርት ቤት ለማስገባት፤ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ፤ መንግስት የሚሰጠውን እርዳታ በልጅዎ ስም ለመቀበል ወይም የሆነ ማንኛውም ልጅዎን ለማሳደግ መደረግ የሚገባውን ሁሉ ለማድረግ የፍርድ ቤት ትእዛዝ አያስፈልጎትም። የፍርድ ቤት ትእዛዝ በሌለበት፤ ማንኛውም ወላጅ፡ ልጁን የሚመለከት ማንኛውንም ውሳኔ ሊወስድ ይችላል።

## ከሌላኛው ወላጅ የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ ለማግኘት፤ በፍርድ ቤት የተወሰነ የልጅ አሳዳጊነት ትእዛዝ ያስፈልገኛልን?

አያስፈልጎትም። የልጅ አሳዳጊ እርስዎ ኖት የሚል የፍርድ ቤት ትእዛዝ (custody order) ባይኖሮትም፤የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ እንዲሰጦት ማመልከት መጀመር ይችላሉ። የፍርድ ቤት ትእዛዝ (custody order) በሌለበትም፤ ልጆቹ በአብዛኛው አብረው የሚኖሩት ወላጅ ነው **አሳዳጊ** (custodian) የሚባለውና (የልጅ ማሳደግያ ገንዘብ (child support) የሚቀበለው ።

## የልጅ አሳዳጊ መብት እንዲሰጠኝ እንዴት ነው ጉዳዬን ፍርድ ቤት የማቀርበው?

በ ኦንላይን ወደ https://www.probono.net/dccourts/familycourt/ ገብተው አሳዳጊነትን የሚመለከት አቤቱታ Complaint for Custody የሚለውን ፎርም መሙላት ይችላሉ። ይህንን ፎርም ለሞምላት ችግር ካለቦት፤ በስልክ ቁጥር 202-879-0096 ደውለው ከቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስን በርስ የማገዝ ማእከል ጋር ተገናኙ።። ይሄው የቤተሰብ ፍርድ ቤት በአሁኑ ግዜ በስልክ ብቻ ስለሆነ የሚገኘው የሚፈልጉትን እርዳታ በስልክ ማግኘት ይችላሉ። ፎርሙ አንዴ ከተሞላ በኋላ፤ ከሚከተሉት ሶስት መንገዶች በአንዱ ለፍርድ ቤት ሊያቀርቡት ይችላሉ፣

- የሚከፍሉት ገንዘብ ከሌለ ወይም መክፈል የሚገባዎት ክፍያ ከተነሳሎት፤ በኦንላይን ወደ CaseFileXpress በመግባት ሊያመለከቱ ይችላሉ። ግን የሚከፈለውን ገንዘብ መክፈል ካለቦት፤ የኬዝፋይልኤክስፕሬስ ፋይል እንዲከፍትሎት የቤተሰብ ፍርድቤቱን (Family Court) ያነጋገሩ።

- አቤቱታዎን በቀጥታ ወደ FamilyCourtcic@dcsc.gov ኢሜል ማደረግ ይችላሉ በተለይ በፋይሎ ውስጥ የተፈቀደ ማመልከቻ Application to Proceed In Forma Pauperis ካሎት አያይዘው መላክ ይችላሉ።

- ከክፍያ ነጻ ለመሆን ካልቻሉ፤ ቅሬታዎን ወደ ኬዝፋይሌክስፕሬስ( CaseFileXpress) መላክ ይችላሉ። ይህም ማለት መጀመርያ ከቤተሰብ ፍርድቤት (Family Court) ጋር ተገናኝተው የጉዳዩን መዝገብ ማስያዝ አለቦት።

# አስቸኳይ የሆነ የአሳዳጊነት መብት እንዲሰጦት ስለመጠየቅ

## አስቸኳይ የሆነ የአሳዳጊነት መብት እንዲሰጠኝ መቼ መጠየቅ አለብኝ?

ዳኛ፤ ፈጣን የሆነ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነና የልጅዎ ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ ነው ብለው የሚያምኑ ከሆነ አስቸኳይ የሆነ የአሳዳጊነት መብት ክስ ማስገባት አለብዎት። ለምሳሌ፣ ሌላኛው ወላጅ ልጅዎ ላይ ጥቃት እንደፈጸመ፣ ችላ እንዳለ፣ ወይም አግቷል ብለው የሚጠረጥሩ ከሆነ፣ የአስቸኳይ ጊዜ መፍትሔ ማግኘት ይችላሉ።

## በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት አስቸኳይ የአሳዳጊነት መብጥ ጥያቄ እንዴት ማቅረብ እችላለሁኝ?

የቤተሰብ ፍርድ ቤት (The Family Court)፤ ከሩቅ በስልክ ወይም በቪድዮ የሚሰሙ አስቸኳይ ችሎቶችንመስማቱንና የፍርድ ቤት ትዕዛዞችን ማስተላለፉን ቀጥሎበታል። በቴሌኮንፈረንስ በኩል አስቸኳይ ችሎቶች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ምንም ዓይነት ነባር የአሳዳጊነት ክስ መዝገብ ካልተከፈተ፣ የአሳዳጊነት ቅሬታ ማቅረብ (Complaint for Custody) ፣ የ ጊዜያዊ የአሳዳጊነት ጥያቄ (Motion for Temporary Custody) በመሙላት ወደ የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማዕከላዊ የመቀበያ ማዕከል (Family Court's Central Intake Center) በኢሜይል FamilyCourtcic@dcsc.gov ላይ ይላኩ ወይም በአካል ይሂዱ።

ጊዜያዊ የአሳዳጊነት መብት ጥያቄው (Motion to Temporary Custody) አስተቸኳይ እንደሆነ መጥቀስ አለብዎት።

ከዚህ ቀደም የተሰጠ የአሳዳጊነት መብት ትእዛዝ ካለ፣ የአሳዳጊነት ትዕዛዝ የመቀየሪያ ጥያቄ (Motion to Modify Custody) ፣ ቅጽን መሙላትና ወደ ቤተሰብ ፍርድቤት ማዕከላዊ የመቀበያ ማዕከል (Family Court's Central Intake Center) በአካል ወይም በኢሜይል FamilyCourtcic@dcsc.gov መላክ እና የአሳዳጊነት ትዕዛዝ መቀየሪያ ጥያቄው አስቸኳይ እንደሆነ መናገር አለብዎት።

ጊዜያዊ የአሳዳጊነት መብት ጥያቄው (Motion to Temporary Custody) አስተቸኳይ እንደሆነ መጥቀስ አለብዎት።

ፍርድ ቤቱ የእርስዎን አስቸኳይ ጥያቄ አንዴ ከተቀበለ በኋላ፣ አንድ ዳኛ ጥያቄውን ይመለከታል እና በስልክ ችሎት መስማት አስፈላጊ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ይወስናል። ፍርድ ቤቱ ድንገተኛ የሆነ ሰሚ ችሎት ለማድረግ የወሰነ ከሆነ ሁለቱም ወላጆች እንዲገኙ ይጠየቃሉ።

## የኮቪድ (COVID-19) ቀውስ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ ጉዳዬ በፍርድ ቤት ሲሰማ የሚያግዘኝ ህጋዊ ድጋፍ ላገኝ እችላለሁን ?

አዎን። ከቤተሰብ ሕግ ድጋፍ ሰጪ አውታረመረብ (Family Law Assistance Network) ("FLAN") (የዲሲ ጠበቆች ነፃ የሕግ አገልግሎት ሰጪ ማዕከል (D.C. Bar Pro Bono Center) ፣ ሌጋል ኤድ (Legal Aid) ፣ እና የዲሲ አዋጭ ሕግ ድርጅት (D.C. Affordable Law Firm) ጥምረት የሆነ) ወላጆችን አስቸኳይ አሳዳጊነት መብት ችሎቶች ላይ (በስልክ) ጥብቅና ሊቆሙ ይችላሉ። ወላጆች በ (202) 844-5428 ላይ በመደወል ጥብቅ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ።.

### የአሳዳጊነት መፍትሔ መጠየቅ በተጨማሪ፣ የልጄ ሌላኛው ወላጅ ልጄን አደጋ ውስጥ እየከተታት ነው ብዬ የማስብ ከሆነ ሌላ ምን ማድረግ እችላለሁኝ?

በልጅዎ ላይ አንድ ዓይነት ነገር እየተፈጸመ ነው ብለው ከጠረጠሩ፤ በስልክ ቁጥር (202) 442-610ወደ ልጅና ቤተሰብ አገልግሎት (Child and Family Services Agency) መደወል ይችላሉ ወይም በልጅ ላይ በደል እየተፈጸመ ነው ብለው ሙሉ ክፍት ወደሆነው አስቸኳይ መስመር በ ስልክ ቁጥር (202) 671-7233በመደወል ሪፖርት ሊያድረጉ ይችላሉ።

## የአሳዳጊነት ትእዛዝን ማሻሻል

### የአሳዳጊነት ትእዛዝ አንዴ ከጸደቀ በኋላ መቀየር ይቻላልን?

አዎን። ፍርድ ቤቱ፤ በወላጆቹ ፈቃድ ወይም በፍርድ ቤት በቀረበና በተወሰነ ጉዳይ፤ ቋሚ የሆነ የአሳዳጊ ትእዛዝ ካጸደቀ በኋላ፤ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ወላጆች ስምምነት ወይም አንዱ ወላጅ የአሳዳጊነት ለውጥ እንዲደረግ Motion to Modify Custody ሞልቶ ባቀረበው አቤቱታ መሰረት፤ ትእዛዙ ሊቀየር ወይም ሊሻሻል ይችላል።

### ፍርድ ቤቱ የአሳዳጊነትን ጉዳይ ለማሻሻል(Motion to Modify Custody) እንዴት ነው የሚወስነው?

ቋሚ የነበረ የአሳዳጊነት ትእዛዝ እንዲሻሻል ወይም በላዩ ላይ ለውጥ እንዲደረግ፤ ጠያቂው ወላጅ፤ በሁኔታዎች ላይ ትልቅ ለውጥ እንደተከተለና የአሳዳጊነት ሁኔታ ላይ ለውጥ ወይም መሻሻል ከተደረገ ለልጆቹ ጥቅም መሆኑን ፍርድ ቤቱን ማሳመን አለበት። ስለዚህ የተጠየቀው ለውጥ፤ ለልጆቹ ጥቅም መሆኑን ፍርድ ቤቱ በቋሚነት የተመዘገቡትን አስራ ሰባት የጠቀሜታ ማሳያዎችን best interest factors መመርመር አለበት።

### በኮቪድ-19 (COVID-19) ወቅት የአሳዳጊነት ጉዳይን ለማስተካከል ወይም ለማሻሻል አቤቱታ ለማቅረብ እችላለሁን?

አዎን። ይህንን የአሳዳጊነትን ጉዳይ ለማሻሻል Motion to Modify Custody የሚለውን ፎርም ከሶስቱ ውስጥ በአንዱ ሞልተው በኦንላይን ይላኩ።

- ይህንን የአሳዳጊነትን ጥያቄ ለማሻሻል በ Case File Xpress ውስጥ በመግባት ማመልከቻ መሙላት ይቻላል። የሚከፈለው ዋጋ እንዲነሳሎ የሚያደርግ ፈቃድ ከሌሎት ወይም እንዲነሳሎ ብቁ ሆነው ካልተገኙ ግን $20 መክፈል አለቦት።

- ምንም ዋጋ ላለመክፈል የተፈቀደሎት ፋይል ውስጥ ካለ፤ ይህንኑን አሳዳጊነትን ለማሻሻል የተባለውን ፎርም ሞልተው ከተፈቀደሎት ፋይል ጋር አያይዘው ወደ FamilyCourtcic@dcsc.gov በኢሜል ይላኩ።

- በዲሲ የላይኛው ፍርድ ቤት በ ክፍል JM-540 ወደ ሚገኘው የቤተሰብ ፍርድ ቤት በአካል ሂደው ማመልከት ይችላሉ።

# <u>ጉብኝት/ጥየቃ</u>

## ከፍርድ ቤት ምን ዓይነት የጉብኝት መብቶችን ማግኘት እችላለሁ?

በእናትና በልጆች መካከል የሚደረግ ግንኙነት፤ ሶስተኛ አካል በታዛቢነት በሚገኝበት ሊሆን ይችላል ወይም ታዛቢ በሌለበት ሊሆን ይችላል።

- ታዛቢ ወይም ሶስተኛ አካል ባለበት የሚደረግ ግኑኝነት፤ ዳኛው፤ ልጆች ሌላኛውን ወላጃቸውን ለመጠየቅ ሲሄዱ፤ የልጆቹ ደህንነት ሊጠበቅ አይችልም ብሎ ካመነ፤ ግንኙነቱ ታዛቢ ባለበት በ ፍርድ ቤቱ የጉብኝት ማእከል (Court's Supervised Visitation Center) እንዲሆን ሊያዝ ይችላል። . ይህንንም ቦታ ዳኛው፤ መገናኘት የማይፈልጉ ሁለቱ ወላጆች፤ ልጆቻቸውን የሚጥሉበትና መልሰው የሚወስዱበት ቦታ እንዲሆን ያድረጋል። ስለዚህ በዳኛ ትእዛዝም፡፤ ሌሎች ሰዎች እንደ ሶስተኛ አካል ወይም እንደታዛቢ ሊያገለግሉ ሊፈቅድ ይችላል (ለምሳሌ እንደ ታመነ ጓደኛ ወይም የታመነ ዘመድ የመሳሰሉ) ።

- ታዛቢ ወይም ሶስተኛ አካል የሌለበት ጉብኝት፤ ታዛቢ የሌለበት ጉብኝት ሲባል፤ በማታ ሳይሆን በቀን ብቻ የሚደረግ፤ ልጆች የተወሰኑ ሰዓታት ብቻ ከወላጅ ጋር የሚቆዩበት ግዜ ሊሆን ይችላል ወይም የአዳር ቆይታ (በወላጃቸው ቤት የሚያድሩበት ጉብኝት) ሊሆን ይችላል።

እነኚህ ዓይነት ጉብኝቶች በየሰንት ቀናቱ ይደረጋሉ፤ ወይም ጉብኝቶቹ ምን ዓይነት ናቸው ወይም ምን ያህል ግዜ ይቆያሉ የሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙት በሁለቱ ወላጆች የጋራ ስምምንት ወይም የልጆቹን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ወቅቱ የኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ወቅት በሆነበት በአሁኑ ግዜ፤ በፍርድ ቤት የተወሰነውን የልጆች ጉብኝት ትእዛዝ የግድ ማክበር አለብኝን?

ቦታው ስላምና ደህንነቱ የተጠበቀ እስከሆነ ድረስ፤ በተሰጠው የፍርድ ቤት የጉብኝት ትእዛዝ መገዛት አለቦት። ዳኞች፤ በአሁኑ በኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ ወላጆች በተቻለ መጠን እርስበርስ ተረዳድተው ልጆቻቸው ሌላውን ወላጃቸውን የሚጎበኙበትን ትእዛዝ እንዲያከብሩላቸው ይጠብቃሉ።

## በዚህ የኮቪድ (COVID-19) ወቅት፤ ታዛቢ ያለበት የጉብኝት ማእከሉ (Supervised Visitation Center) አሰራር ምን ይመስላል?

ታዛቢ ያለበት የጉብኝት ማእከሉ (Supervised Visitation Center) በአሁኑ ወቅት ታዛቢ ላለበትና በአካል ለመገናኘት የሚያስችለው ዕድል ዝግ ነው።]ታዛቢ ያለበት የጉብኝት ማእከሉ (Supervised Visitation Center) በአሁኑ ግዜ ግብኝቶች ቨርቹዋል( ወይም በስልክና በኮምፑተር) ብቻ እንዲካሄዱ በማመቻቸት ላይ ይገኛል።

## በዚህ በኮቪድ--19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ወቅት፤ የተሰጠኝ የፍርድ ቤት ትእዛዝ፡ ልጆቹ ከሌላው ወላጅ ጋር የሚገናኙበት ታዛቢ ባለበት የጉብኝት ማእከል (Supervised Visitation Center) ነው ካለ ምን ማድረግ አለብኝ?

እስከአሁን ድረስ በቪርቿል የሚደረግ ታዛቢ ያለበት ጉብኝት ገና ካላደረጉ፤ እነዚህን ጉብኝቶች ለማመቻቸት ታዛቢ ያለበት ጉብኝት የሚካሄድበትን ማእከል ደውለው ያነጋግሩ። በአሁኑ ወቅት ወላጆች አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደምንገኝ ሰከን ባለ መንፈስ ማሰብና ማመዛዘን ይኖርባቸዋል። በመሆኑም አማራጮችን መገምገም መቻል አለባቸው። ከሁለተኛው ወገን ጋርም ጉብኝትን በተመለከተ ለመነጋገር ሞክሩ። መወያየት ደህና ይመስለናል።

ደህንነቱ የተጠበቀና ተገቢ የሆኑ ዝግጅቶች የተደረገበት ቦታ ታዛቢ ካለው የጉብኝት ቦታ (Supervised Visitation Center) ውጪ ሊገኝ ካልቻለ፤ የአሳዳጊነትን ትእዛዝ በተመልከተ ለውጥ የሚሻው ወላጅ Motion to Modify Custody Order የተሰኘውን ፎርም መሙላት አለበት።

## የአሳዳጊነት ትእዛዙ (custody order) ፤ በአንድ በተወሰነ ቦታ፤ ሶስተኛ አካል በታዛቢነት ባለበት ማእከል፤ አንዱ ወላጅ  ለሌላው ወላጅ ልጁን ለተወሰነ ግዜ

### የሚያስረክብ ከሆነና ወቅቱ የኮቪድ-19 የወረርሽኝ በሽታ ወቅት ከሆነ ምን ማድረግ አለብኝ?

በተቻለ መጠን የሁኔታውን አስቸጋሪነት ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፤ በዚህ የወረርሽኝ ግዜም ጉብኝት መቀጠል ስላለበት በተቻለ መጠን ደህንነት የሚጠበቅበትና የተለመደው የልጅ መለዋወጥን በሌላ ዓይነት አማራጭ መንገድ መቀየር ይቻላል። ለምሳሌ ልውውጡ በፖሊስ ጣብያ ውስጥ እንዲሆን ማድረግ ይችላሉ ወይም በሚያምኑት ጓደኛ ፊት ሊሆን ይችላል።

ታዛቢ ከሚገኝበት የጉብኘት ማእከል ውጪ፤ ተገቢና ደህንነቱ የተጠበቀ የመለዋውጥ ቦታ ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ ከተገኘ፡ የተደረገውን የአሳዳጊነት ትእዛዝን ለማሻሻል (Motion to Modify Custody Order) በሚል ጥያቄ ስር ጉዳዮን እንደገና ፍርድ ቤት ያቅርቡ።

# አሳዳጊነትንና ጉብኝትን በተመለከተ የሚደረግ እርዳታ

## የኮቪድ-19 (COVID-19) የወረርሽኝ በሽታ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ የአሳዳጊነትን ጉዳይ በተመለከተ የት ነው ህጋዊ እርዳታ ማግኘት የምችለው?

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ ውስጥ ያለው ሊጋል ኤድ ሶሳይቲ (Legal Aid Society) በመባል የሚታወቀው የህግ ክፍል፤ ይህንን የአሳዳጊነት ጉዳይ በተመለከተ ለወላጆች ምክር ሊሰጡ የሚችሉ ጠበቃዎች አሉት። ጽህፈት ቤታችን በዚህ በኮቪድ-19 በሽታ ምክንያት በአሁኑ ወቅት ከደንበኞቻችን ጋር በአካል ለመገናኘት የምንሰጠው ቀጥሮ ዝግ ቢሆንም፤ በስልክ ቁጥር (202) 628-1161 በመደወል ወይም አንላይን በመግባት አገልግሎታችንን ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ።

በተጨማሪም የቤተሰብ የህግ እርዳታ ኔትዎርክ ወይም ፍላን (Family Law Assistance Network (FLAN) ) በመባል የሚታወቀውን ድርጅት (የዲሲ የባር ፕሮ ቦኖ ማእከል (D.C the. Bar Pro Bono Center) ፣ ሊጋል ኤድ (Legal Aid) እንዲሁም የዲሲ የቅናሽ ዋጋ የህግ ተቋም ትብብር (D.C. Affordable Law Firm) ትብብር በስልክ ቁጥር (202) 844-5428 በመደወል እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ።

የክሶን ማመልከቻ፤ ፍርድ ቤት የሚናገሩትን እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ጽሁፍ የሚያረቅሎትና መዝገብ የሚያስገዝሎት እርዳታ ከፈለጉ ደግሞ በስልክ ቁጥር (202) 879-0096 በመደወል ከ ቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ በራስ እርዳታ ማእከል (Family Court Self-Help Center) ጋር ተገናኙ።